## በቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የመጀመሪያ መንፈቅ ዓመት የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ትምህርት

### ሞዴል ፈተና የ2016 ዓ.ም

## አጠቃላይ ትዕዛዝ፤-

**የተፈቀደው ሰዓት፤- 1ሰዓት**

ውድ ተፈታኞች ይህ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ 60 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ያሰጣል። ውድ ተፈታኞች በፈተና ላይ የተሰጡትን ትዕዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል። መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው፤በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ትክክለኛው መልስ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልክ በደንብ መጥቆር አለበት፤የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት።

ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተፈቀደው ሰዓት 1 ሰዓት ነው። ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናው መስራት ማቆም አለብን። ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን።

መኮረጅወይም በፈተና ሰዓት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናውአይያዝለትም፣ፈተናውን እናዳይፈተንም ይደረጋል።ፈተናውን መስራት ከመጀመራችሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት።

**ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም!!!**



LIVEWORKSHEETS

# በቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የመጀመሪያ መንፈቅ ዓመት የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ትምህርት

## ሞዴል ፈተና

***መመሪያ አንድ፤- ከተራ ቁጥር አንድ እስከ አስር ያሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ስለሁነም ምንባቡን በጥሞና በማንበብ የቀረቡትን ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ መልሳችሁን በመልስ መስጫ ቦታው ላይ አጥቁሩ፡፡***

## ምንባብ

በሀገራችን እድሜ መስታወት ነው የሚል የቆየ አባባል አለ፡፡ በልደትና በሞት መካከል ህጻንነት፣ጉርምስና፣ ወጣትነት ፣ጎልማሳነት ሽምግልና፣እርጅና ሁሉም በየተራ ወቅቱን እየጠበቁ ይፈራረቃሉ፡፡ ከህጻንነት እስከ ጉርምስና ያለው የልጅነት ዘመን በየአጋጣሚው የሚታወስ ነው፡፡ እንደገጠመኙ ብዛትና ማነስ፣ጥሩነትና መጥፎነት፣ እንደትዝታው ጥራትና ደብዛዛነት የሚናፍቅ ወይም የሚዘገንን ሊሆን ይችላል፡፡ የአሳዳጊ ወይም የወላጅ ፍቅርን አግኝተው በተስማሚ አካባቢ የሚወለዱና ከሚግባቡት ባልንጀሮች ጋር የሚያድጉ ልጆች ሲነጋ ይቦርቃሉ፤ ጀንበሯ ስታዘቀዝቅ ገና ደንገዝገዝ ሲል እቤት ይገባሉ፤ ሳያስቡ ሳይጨነቁ ይተኛሉ፤ ወፍ ሳይንጫጫ ይነሳሉ፤ እንደገና ይቦርቃሉ… ይህንን ይህንን ሲያስቡት መልካም ትዝታው ከልብ አይጠፋም፡፡ በችግርና መንገላታት፣ በብቸኝነት ጭቆና፣ በህመምና ጉስቁልና የሚያድጉ ደግሞ የዚህ ተቃራኒ ሊሆን ይችላል፡፡

ወደ አዋቂነት የሚያሻግረው የወጣትነት ዘመን ጉርምስና በመጠኑ የሚቀላቀልበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከሦርግ ሦርግ ጨዋታ በደረጃው ከፍ ያለ የህልም ዓለሙ ዓይነት ምኞት እውነተኛ መልኩን ያገኝበታል፤ የተስፋ ቡቃያ ያሸትበታል፤ ልበ ሙሉነት ገኖ ይታይበታል፤ የአዕምሮና የጉልበት ኃይል ይጋጋልበታል፡፡ ቤተሰብ ለመመስረት፣ ዓላማን በተግባር ለመተርጎም የሚዘጋጁበት ወቅትም ነው፡፡ አካባቢን በሚገባ ማወቅ፣ በጎውን ከክፉ መለየትይጀመርበታል፡፡ የሀገርና የወገን ፍቅር ይጎላበታል፡፡

ከዚህ በኋላ ያሉት ወቅቶች መጃጀት እስኪመጣ ድረስ የቤተሰብና የማህበረሰብ ሃላፊነትና አመዛዛኝነት፣ ትዕግስትና እርጋታ ይታይባቸዋል፣ ዕውቀት ይዳብርበታል፣ ብስለት ይንሰራራበታል፡፡ የመጃጀት አጭር ወቅት ድንገት ሲመጣ ደግሞ ከዓመት ዓመት እየተካበ ተከምሮ የኖረው ሁሉ በአዕምሮ ሚዛን መቃወስ ባንዴ ፈርሶ ወደ ህጻንነት ይመለሳል፡፡ በዚህ ጊዜ ዕድሜ መስታወት መሆኑ ይቀርና ጭቃ ማቡኪያ ይሆናል፡፡ እንዲህ ሲሆን ለሰው ልጅ በህጻንነቱ ልዩ መዓዛ ሰጥታ ያስቆነጀችው ተፈጥሮ በገዛ ሥራዋ ላይ አስቀያሚ ሳቋን መሳቅ ትጀምራለች፡፡

**ምንጭ ፤- (መስፍን ኃብተማርያም የቡና ቤት ስዕሎች)**



LIVEWORKSHEETS

1. ምንባቡ መሰረት "ዕድሜ መስታወት ነው" የሚለው አነጋገር ምንን ይገልጻል?

ሀ. ዕድሜ እንደ መስታወት ምስል የሚያንጸባርቅ መሆኑን

ለ. የዕድሜን መስታወትነት እያደር የምንገነዘበው መሆኑን

ሐ. ዕድሜ በረዘመ ቁጥር ሁሉንም ነገር ለመረዳት የሚያስቸግር መሆኑን

መ. ዕድሜ በረዘመ ቁጥር ደጉንም ክፉውንም ለማየት የሚያስችል መሆኑ

2. "ጀንበሯ ስታዘቀዝቅበ ገና ደንገዝገዝ ሲል" የሚለው አገላለጽ የትኛውን ጊዜ ያመለክታል?

ሀ. ለዓይን ያዝ ሲያደርግ

ሐ. ጸሐይ ሳትጠልቅ

ለ. እኩለ ሌሊት ሲሆን

መ. ጨረቃ መውጣት ስትጀምር

3. በምንባቡ መሰረት "የተስፋ ቡቃያ ያሸትበታል" የሚለው አገላለጽ የትኛውን ሀሳብ ይተካል?

ሀ. ሰብል ጎምርቶ ይታይበታል

ሐ. እሸቱ በስሎ ይበላበታል

ለ. ምኞት ወደ ተግባር ይለወጥበታል

መ. የምኞት ደረጃው ከፍ ይልበታል

4. በወጣትነትና በሽምግልና መካከል ያለውን የዕድሜ ዘመን ለመግለጽ ከሚከተሉት መካከል የትኛው የተሻለ ይሆናል?

ሀ. ሰው ምራቁን ዋጥ የሚያደርግበት

ሐ. ሰው ስሜቱን የሚያጋግልበት

ለ. ሰው አገሩን የሚጎበኝበት

መ. ሰው የህይወት አጋሩን የሚፈልግበት

5. ከሚከተሉት መካከል የምንባቡን መልዕክት በተሸለ የሚገልጸው የትኛው ሀሳብ ነው?

ሀ. ወቅቶች በራሳቸው ጊዜ ስለሚፈራረቁ መጨነቅ አይገባም፡፡

ለ. የሰው ልጅ በሚጃጅበት ጊዜ የሚንከባከበው ቤተሰብ ያስፈልገዋል፡፡

ሐ. የሰው ልጅ ተፈጥሮን በአግባቡ ተጠቅሞ ማለፍ አለበት፡፡

መ. ተፈጥሮ ለሰው ልጅ የደስታ ምንጭ ናት፡፡

6. በምንባቡ መሰረት ከህጻንነት እስከ ጉርምስና ያለው የልጅነት ዘመን በደስታ ወይም በችግር የተሞላ ከሚያደርጉ ምክንያቶች ውስጥ የማይጠቀሰው የትኛው ነው?

ሀ. የአሳዳጊ ወይም የወላጅ ፍቅርን ማግኘት ወይም አለማግኘት፡፡

ለ. በተስማሚ ወይም በማይስማማ አካባቢ መወለድ፡፡

ሐ. የሚግባቡትን ባልንጀራ ማግኘት ወይም አለማግኘት፡፡

መ. የቤተሰብ ቁጥር መብዛት ወይም ማነስ፡፡

7. በምንባቡ መሰረት በልደትና በሞት መካከል ያለውን የዕድሜ ሂደት ቅደም ተከተሉ የትኛውን ይመስላል?

ሀ. ህጻንነት፣ወጣትነት፣ጉርምስና፣ጉልምስና፣ሽምግልና፣እርጅና

ለ. ህጻንነት፣ጉርምስና፣ወጣትነት፣ጉልምስና፣ሽምግልና፣እርጅና

ሐ. ህጻንነት፣ወጣትነት፣ጉልምስና፣እርጅና፣ጉርምስና፣ሽምግልና

መ. ህጻንነት፣ጉልምስና፣ጉርምስና፣ወጣትነት፣እርጅና፣ሽምግልና



LIVEWORKSHEETS

8. እንደጸሐፊው አተያይ የልጅነት ዘመን ችግርና መንገላታት፣ ብቸኝነትናጭቆና፣ ህመምናጉስቁልና የተሞላበት ከሆነ ምን ዓይነት ትውስታ ይኖረዋል?

ሀ. አሰልቺ ለ. ደብዛዛ ሐ. ተናፋቂ መ. ዘግናኝ

9. እንደጸሐፊው እምነት ሰው በዕድሜ ባለጸጋ በሆነ ቁጥር ምን ዓይነት ባህሪ ይኖረዋል

ሀ. የማመዛዘን ለ. የመፍዘዝ ሐ. የመቀለድ መ. የመቸኮል

10. ከሚከተሉት መካከል በምንባቡ ውስጥ የምክንያትና የውጤት ትስስር ያለው ዓረፍተነገር የትኛው ነው?

ሀ. መጃጀት እስኪመጣ ድረስ የቤተሰብና የማህበረሰብ ሃላፊነት ይኖራል።

ለ. ወደ አዋቂነት የሚያሻግረው የወጣትነት ዘመን ጉርምስና ነው።

ሐ. ከህጻንነት እስከጉርምስና ያለው ዘመን በየአጋጣሚው የሚታወስ ነው።

መ. በተስማሚ አካባቢ የሚያድጉ ልጆች ነጻነት ስለሚሰማቸው ይቦርቃሉ።

**<u>መመሪያ ሁለት፤- ከ11-40 ድረስ የተለያዩ የቋንቋ ጥያቄዎች ቀርበዋል ። ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ በማስተዋል በማንበብ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሳችሁን በመልስ መስጫ ቦታው አጥቁሩ።</u>**

11. የአንድን ነገር መፈጸምን ወይም መከወንን የሚገልጽ የግስ ዓይነት ምን ይባላል?

ሀ. የመሆን ግስ ለ. የድርጊት ግስ ሐ. አጎላማሽ መ. ሁሉም

12. .ከሚከተሉት መዋቅሮች መካከል ስማዊ ሀረግ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ.ገበሬው ያመረተው ጥሩ ምርት ሐ. ለም የእርሻ መሬት

ለ. እንደ እርግብ የዋህ መ. መልከ መልካም ልጃገረድ

13. በአማርኛ ቋንቋ የዐ.ነገር አወቃቀር በ-------እና በ------- የሚመሰረት ነው።

ሀ. በቅዕልና በገላጭ ሐ. በገላጭ ግስች

ለ. በመስተዋድድን በመስተፃምር መ. በስምና በግስ

14. "ነው" የሚለውን ግስ በአንድ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ቢገባ ዓረፍተ ነገሩን ከጊዜ አንጻር ሊወክለው የሚችለው ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ የትኛው ነው?

ሀ. የአሁን ጊዜን ለ. የትንቢት ጊዜን ሐ. የኃላፊ ጊዜን መ. የቅርብ ኃላፊ ጊዜን

15. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ለገቢር ግስ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው ዓረፍተ ነገር የትኛው ነው?

ሀ. አየለ በሩን መታ። ሐ. መስታወቱ በአልማዝ ተሰበረ።

ለ. ስጋው በሰናይት ተጠበሰ። መ. ልብሱ በአሊ ተቀደደ።

16. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ‹እነ-› የሚለውን አብዥ ቅጥያ የሚወስደው ቃል የትኛው ነው?

ሀ. መፅሐፍ ለ. ምሁር ሐ. ቤት መ. ተሾመ



LIVEWORKSHEETS

17. ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ቃላት መካከል የተግብሮ ቃል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ገዛ ለ. ተገዛ ሐ. ገዛች መ. ገዙ

18. ከሚከተሉት ውስጥ አንድ ድርጊት ከቅርብ ጊዜ በፊት የተፈጸመ መሆኑን የሚገልጽ የጊዜ አይነት የቱ ነው?

ሀ. የትንቢት ጊዜ ሐ. የቅርብ ኃላፊ ግዜ

ለ. የሩቅ ኃላፊ ጊዜ መ. የኃላፊ ጊዜ

19. ሁለት ዓ.ነገር መሆን የሚችሉ ቅንጅቶች በአያያዦች በአንድ ዓ.ነገር ተጠቃለው ሲቀርቡ ምን ዓይነት ዓ.ነገር ይባላል ?

ሀ. ነጠላ ዓ.ነገር ለ. ድብልቅ ዓ.ነገር ሐ. ድርብ ዓ.ነገር መ. ድርብ ድብልቅ ዓ.ነገር

20. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በድርብ ቃል የተመሰረተው ዓረፍተ ነገር የቱ ነው?

ሀ. መጥፎ ባህርይ ያላቸው ልጆች አድገው ለወገንም ለአገርም አይጠቅሙም።

ለ. የአንድ ታዳጊ ነገረስራው ካላማረ የወደፊት ሕይወቱ የተበላሸ ይሆንበታል።

ሐ. ቤተሰብ ለአንድ ልጅ የወደፊት ሕይወት ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ ናቸው።

መ. የልጆች ወጣ ወጣ ማለት ከመጥፎ ልማድ ጋር ካልተያያዘ ችግር የለውም።

21. የማንኛውም ቋንቋ መዋቅር መሰረቱ ምንድን ነው?

ሀ. ቃላት ለ. ድምጽ ሐ. ምዕላድ መ. ቃል

22. ‹‹የአማርኛ ሰዋሰው ትምህርት በተለያዩ ደረጃ በትምህርት ቤት ውስጥሲሰጥ ቆይቷል፤-----------------ለትምህርት የሚረዱ አጋዥ የሰዋሰው መፅሀፍት በየደረጃው እየተዘጋጁ ሲቀርቡ ብዙ አይታይም።በክፍት ቦታው ሊገባ የሚችለው አያያዥ የተኛው ነው?

ሀ. ስለዚህ ለ. አለበለዚያ ሐ. ስለሆነም መ. ይሁን እንጂ

23. በአንድ አንቀፅ ውስጥ የሚተላለፋው ሀሳብ ጎልቶ እንዲታይ ለማድረግ የሚቻልበት የአንቀፅ ባህሪ ምን ይባላል?

ሀ. አንድነት ለ. ውህደት ሐ. አጽንዖት መ. ሀ ና ሐ

24. ከዚህ በኃላ ብቸኝነት ቀርቶብኝ <u>ውሃ አጣጭ</u> ልፈልግ። የተሰመረበት ቃል ዓውዳዊ ፍቺ ምንድን ነው?

ሀ. ሠራተኛ ለ. እህት ሐ. እናት መ. የትዳር አጋር

25. እህል ውሃ ቀመሰ የሚለውን አገላለጽ ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ከየትኛው ጋር በትርጉም ሊስማማ ይችላል?

ሀ. አፋን አሟሸ ለ. አፋን አበሰ ሐ. አፋን ዘጋ መ. አፋን አጣፈጠ



LIVEWORKSHEETS

26. "ልጁ ምሳውን በላ። ልጁ አሁን እጁን ይታጠባል። ልጁ ወደ ትምህርት ቤት ከሰዓት በኃላ ይሄዳል።"እነዚህ በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ የተጻፉበት ጊዜ በቅደም ተከተል በትክክል የያዘው አማራጭ የትኛው ነው?

ሀ. የአሁን ጊዜ፣ የትንቢት ጊዜ፣ የኃላፊ ጊዜ

ለ. የኃላፊ ጊዜ፣ የአሁን ጊዜ፣ የትንቢት ጊዜ

ሐ. የትንቢት ጊዜ፣ የአህን ጊዜ፣ የኃላፊ ጊዜ

መ. የአሁን ጊዜ፣ የአላፊ ጊዜ፣ የትንቢት ጊዜ

27.ከበደ የትምህርት ዝንባሌው ዝቅተኛ ነው። ለተሰመረበት ቃል በፍቺ የሚስማማው የትኛው ነው?

ሀ. ጭንቀቱ ለ. ዕቅዱ ሐ. ጥረቱ መ. ፍላጎቱ

28.ፈዛዛ ብሎ ደማቅ ቢል አናት ብሎ -------- ይላል።

ሀ. መሀል ለ. ጣሪያ ሐ. ግርጌ መ. ጎን

29.ከሚከተሉት ውስጥ የብዛትንና የባለንብረትን ምዕላድ አጣምሮ የያዘው ቃል የቱ ነው?

ሀ. ጓደኞዬ ለ. ባልደረባዬ ሐ. ወንድሜ መ. ባልደረቦቼ

30.ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት መካከል -ኣማ የሚለውን አብገር ምዕላድ የሚወስደው የቱ ነው?

ሀ. ብርድ ለ. ሰው ሐ. በሬ መ. ሀገር

31.ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በግል አስተያይት ላይ የተመሰረተው የትኛው ነው?

ሀ. የአካባቢ ብክለት የጤና ችግር ያስከትላል ።

ለ. አልኮል ለሆድ ቁርጠት መደሓኒት ሳይሆን አይቀርም።

ሐ. ፀሐይ የብርሃንና የሙቀት ምንጭ ናት።

መ. ትምህርት ለአንድ ሀገር ዕድገት መሰረት ነው።

32.ቀጥሎ ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ የንግግር ክሂልን ለማዳበር ከሚረዱ ስልቶች መካከል ልዩ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ቃለ መጠይቅ ለ. የቃል ሪፖርት ሐ. ጭውውት መ. የጹሁፍ ሪፖርት



LIVEWORKSHEETS

33.ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ጭውውት ትክክል **ያልሆነው** የቱ ነው?

ሀ. ለጭውውት ስንቀርብ ስብዕናን ማሟላት/ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

ለ. የሀሳብ ልውውጥ ቢኖርም ሀሳቡን እየቋጨ መሄድ ያስፈልጋል፡፡

ሐ. ጭውውቱ ፍሬያማ እንዲሆን ጥረት ማድረግ አለብን፡፡

መ. በጭውውት ላይ ያልገባን ሀሳብ ካለ መጠየቅ አስፈላጊ አይደለም፡፡

34.የቋንቋ መዋቅር ከትልቅ ወደ ትንሽ ትክክለኛ ቅደም ተከተልን የያዘው አማራጭ የቱ ነው?

ሀ. ድምጽ፣ሐረግ፣ ቃል፣ ዓረፍተ ነገርና አንቀጽ

ለ. አንቀጽ፣ ዓረፍተነገር፣ ቃል፣ ሐረግና ድምጽ

ሐ. ድምጽ፣ ቃል፣ ሐረግ፣ ዓረፍተ ነገርና አንቀጽ

መ. አንቀጽ፣ ዓረፍተ ነገር፣ ሐረግ፣ ቃልና ድምጽ

35.ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክለኛ የሃሳብ ቅደም ተከተል ያለው አንቀጽ ለማስገኘት እንዴት መሆን አለበት::

ሀ. አረጋሽ ሻንጣዋን ይዛ ታክሲ ውስጥ ገባች፡፡

ለ. ትንሽ እንደተራመደች መገናኛ መገናኛ እያለ አንድ ታክሲ አጠገቧ ቆመ፡፡

ሐ. ቅዳሜ ጠዋት አረጋሽ ልብሶቿን በሻንጣ ከታ ደህና ዋሉ ብላ ወጣች፡፡

መ. ትንሽ እንደሄደች ታክሲውን እንዲያቆምላት ጠይቃ ወረደች፡፡፡፡

ሀ. ሀ፣ለ፣ሐ፣መ ለ. ሐ፣ለ፣ሀ፣መ ሐ. ሐ፣ለ፣መ፣ሀ መ. መ፣ለ፣ሀ፣ሐ

36.ከሚከተሉት ውስጥ የውይይት አቀራረብ መመሪያ **ያልሆነው** የትኛው ነው?

ሀ. የውይይቱን ጭብጥ በቅደም ተከተል ማቅረብ፡፡

ለ. በታቻለ መጠን ተደራሲያንን በአገላለጽ ማርካት፡፡

ሐ. ውይይት ፍሬያማ እንዳይሆን ጥረት ማድረግ፡፡

መ. ተደራሲያንን በጥሞናና በሥነ-ሥርዓት ማመስገን፡፡

37.ከሚከተሉት የሐረግ ዓይነት ውስጥ መሪው ቀኝ ወይም ግራ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

ሀ. ስማዊ ሐረግ ለ. ግሳዊ ሐረግ ሐ. መስተዋድዳዊ ሐረግ መ. ቅጽላዊ ሐረግ



LIVEWORKSHEETS

38.ከሚከተሉት ውስጥ ከቋንቋ መዋቅር አንዱ ሲሆን አንድ ሃሳብን ብቻ በያዙ ዓረፍተ ነገሮች ቅንጅት አማካኝነት የሚመሰረት ነው፡፡

ሀ. ቃል ለ. ሐረግ ሐ. ዓረፍተ ነገር መ. አንቀጽ

39.ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ጠብቆና ሳልቶ ሲነገር የተለያየ ትርጉም ሊሰጥ የሚችለው ቃል የቱ ነው

ሀ. ሄደ ለ. ጻፈ ሐ. ጠላ መ. ተጫወተ

40.ጭንቀት ለአእምሮና አካላዊ ጉዳት ይዳርጋል፡፡ በሚለው ዓ.ነገር ውስጥ ለውጤቱ መንስኤ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. አካላዊ ጉዳት ለ. የአእምሮ መታወክ ሐ. ጭንቀት መ. ጉዳት

41.ንግግር አያውቅም ለሚለው አገላለጽ ትክክለኛ ፍቺ ሊሆን የሚችለው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

ሀ. ቋንቋ ባለመማሩ ሲናገር አንደበቱን ይይዘዋል፡፡
ለ. የመስማትና የመናገር ችሎታ የለውም፡፡
ሐ. ቃላት ሳይመርጥ አፉ እንዳመጣለት ይናገራል፡፡
መ. ገና አፉን አልፈታምና ንግግር አይችልም፡

42.ከሚከተሉት ዓ.ነገር መካከል ስህተት የሌለበት አማራጭ የትኛው ነው?

ሀ. እንጀራ የጥቁር ጤፍ እወዳለሁ፡፡
ለ. የጤፍ በወጥ ጥቁር እንጀራ እወዳለሁ፡፡
ሐ. የጥቁር እንጀራ ጤፍ እወዳለሁ፡፡
መ. የጥቁር ጤፍ እንጀራ በወጥ እወዳለሁ፡፡



LIVEWORKSHEETS

***<u>መመሪያ ሶስት</u>*** **፣- ከተራ ቁጥር 41-55 ድረስ ያሉት ጥያቄዎች የተለያዩ ስነ-ጽሑፋዊ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መሰረት አድርገው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ በጥሞና በማንበብ እንደየአጠያየቃቸው ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡**

43.ሽቶዋ ያውዳል፡፡ ጉራማይሌ የተነቀሱት ጥርሶቿ እንደ እንቁ ያበራሉ፡፡ከደረቱ ክፍትየሆነ ሹራብ ጣል አድርጋለች፡፡ያንገት ጌጧም ከጡቶቿ መሃል እንደ ከዋከብት ብልጭ ብልጭ ይላሉ፡፡ይህ ፅሁፍ ለየትኛው ድርሰት ምሳሌ ይሆናሉ፡፡

ሀ. ለተራኪ ድርሰት  ለ. ለስዕላዊ ድርሰት  ሐ. ለአመዛዛኛ ድርሰት  መ. ለገላጭ ድርሰት

44. ከሚከተሉት አማራጮች አንዱ በአጭር ልቦለድ ውስጥ **<u>የማይካተት</u>** ነው::

ሀ. ብዙ ገጸ-ባህሪያትን ያሳትፋል፡፡  ሐ. ቅርጹ ውስን ነው፡፡

ለ. ነጠላ መልዕክት ያስተላልፋል፡፡  መ. መቼቱ ጠባብ ነው፡፡

45.ከልቦለድ ዘዴዎች መካከል በታሪክ ሂደት ወደ ፊት ለሚፈጸም ድርጊት አጋጣሚ ወይም ሁኔታ ፍንጭ የሚሰጠው የቱ ነው?

ሀ. ገለጻ  ለ. ምልሰት  ሐ. ንግር  መ. ምልልስ

46.አንድን ድርጊት ወይም ሁነትን አስመልክቶ በጊዜና በቦታ ቅደም ተከተል መሰረት አድርጎ የሚያቀርብ የድርሰት አይነት ምን ይባላል?

ሀ. ተራኪ ድርሰት  ለ. ገላጭ ድርሰት  ሐ. አወዳዳሪ ድርሰት  መ. ስዕላዊ ድርሰት

47.ከሚከተሉት መካከል አፋዊ ስነ-ጽሁፍ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ግጥም  ለ. ልቦለድ  ሐ. ኢ-ልቦለድ  መ. አፈ-ታሪክ

48.የአንድ ድርሰት አጠቃላይ መዋቅር ለማወቅ የሚያገለግል ንድፍ ምን ይባላል?

ሀ.አንቀጽ  ለ. መንደርደሪያ  ሐ. አስተዋጽዖ  መ. መደምደሚያ

49.በአንድ ድርሰት ውስጥ የገሃዱን አለም መስለው የሚጫወቱ አካላት-------ይባላሉ፡፡

ሀ.ደራሲያን  ለ. ገፀባህርያት  ሐ. አንባቢያ  መ. ተደራሲ

50.አዕምሮ እንዲቀላጠፍ ፣ ጥልቅ የሆነ የማሰብ ችሎታ እንዲኖርና ነገሮችን በቀላሉ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር የሚረዳው ጥበብ የትኛው ነው?

ሀ. ድርሰት  ለ. ትወና  ሐ. ቅኔ  መ. ቃላዊ ግጥም



LIVEWORKSHEETS

51.ከሚከተሉት አንዱ ከቃላዊ ግጥም ውስጥ አይመደብም ።

ሀ. ፉከራ ለ. ሽለላ ሐ. የግጥም መድብል መ. ሙሾ

52.ኩታ አለባበሱን ማነው ያስተማረሽ፣

ማጣፋቱንማ ታውቂበታለሽ ። የዚህ ቅኔ ወርቁ የቱ ነው ነው?

ሀ. ኩታ አለባበሱን።

ለ. የኩታን አለባበሱን ታውቂያለሽ።

ሐ. ማገዳደሉን ተክነሽበታል።

መ. ማጣፋቱን ታውቂያለሽ።

53. ቸሩ አባታችን ለሁሉም ሲያበላ፣

ይገራማል አንዳንዴ አይሰጥም ከጠላ። የዚህ ቅኔ ህብረ ቃሉ የቱ ነው?

ሀ. ለሁሉም ለ. ከጠላ ሐ. አይሰጥም መ. አባታችን

54. አምና ብጠይቅሽ ልጅ ነው ብለሽኛል

ዘንድሮ በተራሽ ---------------------። የዚህ ቃላዊ የፍቅር ግጥም ሊያሟላ የሚችለው ቃል የቱ ነው?

ሀ. ተዝናንተሽብኛል ለ. ወፋፍረሽብኛል ሐ. ተኩራርተሽብኛል መ. አርጅተሽብኛል

55.በቃላዊ ግጥም ውስጥ ስለ ቡሄ በሉ የግጥም አይነት ትክክል የሆነው ከሚከተሉት ውስጥ የቱ ነው?

ሀ. በስንኝ ከሶስት እስከ አምስት ቀለሞችን መያዙ

ለ. በስንኝ ከአምስት እስከ ዘጠኝ ቀለሞችን መያዙ

ሐ. በስንኝ ከሶስት እስከ ስድስት ቀለሞችን መያዙ

መ. በስንኝ ከሶስት እስከ ሰባት ቀለሞችን መያዙ

56.ስለ ቃላዊ ግጥም ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ማህበራዊ አጋጣሚዎችን ማህበራዊ አውድን መነሻ የሚያደርግ ነው።

ለ. በሰለጠነውም ባልሰለጠነውም ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኝ ነው።

ሐ. የሕይወታችንን መልኮች የማያንጸባርቅ ዘርፍ ነው።



LIVEWORKSHEETS

መ. ከትውልድ ወደ ትውልድ በጽሁፍ የሚተላለፍ ነው።

57.አንድን ንባብ ከማንበባችን በፊት ቅድመ ንባብ ተግባራትን መተግበር አለብን። ስለሆነም ከሚከተሉት የቅድመ ንባብ ተግባር ያልሆነው ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ የቱ ነው?

ሀ. ያለፈውን ማስታወስ
ሐ. ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ያለን ዝምድና መፈተሽ
ለ. ርዕሰ ጉዳዩን መተዋወቅ
መ. ስለ ርዕሰ ጉዳዩ መገመት

58.እንጀራ የሚለው ቃል በፍካሬያዊ ፍቺው የገባው በየትኛው ዓ.ነገር ነው?

ሀ. ልጅቷ እንጀራ እየጋገረች ነው።
ለ. እንጀራ በወጥ የተለመደ ኢትዮጵያዊ ምግብ ነው።
ሐ. ወንድማችን እንጀራ ፍለጋ ከአገር አገር ይንከራተታል።
መ. ዛሬ እንጀራ የመብላት ፍላጎት የለኝም።

***መመሪያ አራት ፥- ከተራ ቁጥር 57-60 ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ግጥም ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ግጥሙን በትኩረት ካነበባችሁ በኃላ በእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ተገቢውን መልስ ምረጡ።***

እንደ ዳመና ጓል ታይቶ እንደሚበ
የአንድ አፍታ ክስተት ነው ሕይወት ሲተነተን።
በዓለም ብዙ ሆኗል አልፏል ተከውኖ፣
አሻራ እየተወ ነው ነበርን ሆኖ።
በጊዜ ስንክሳር ታሪክ ሆኖ ፋና፣
መልካም ሥራ አይሞትም ሟችን ያሸኝና።
ጊዜ ሳያሸራቸው ሳይገታቸው ድንበር፣
ታሪክ ሲሆኑ ክብር ሀቅና ቁም ነገር።
ይቺን ጥቂት ነገር መሥራት እያቃተው፣
ከንቱ ይቀራል ሰው መታሰቢያ ሳይተው።

ምንጭ፥- የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር (1999)።የዘመን ቀለማት ። ገጽ 53 በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ።

59.ከላይ የተጻፈውን ግጥም ከሚከተሉት ምሣሌያዊ አነጋገሮች በየትኛው ማጠቃለል ይቻላል?

ሀ. ለስሟ መጠሪያ ቁና ሰፋች።
ለ. ስም ከመቃብር በላይ ይውላል።
ሐ. ጊዜ ሲያመልጥ ራስ ሲመለጥ አይታወቅም።



LIVEWORKSHEETS

መ. ሳይቀር ሞቴ ክፉ መስራቴ።

60.በግጥሙ ውስጥ ስንት ስንኞች አሉ?

ሀ. አምስት ለ. ስድስት ሐ. ስምንት መ. አሥር

61.በግጥሙ አራተኛ ስንኝ መነሻ ሐረግ ከሚከተሉት የትኛው ነው?

ሀ. አሻራ እየተወ "ነው" ሐ. አሻራ እየተወ

ለ. "ነው" "ነበር"ን ሆኖ መ. "ነበር"ን ሆኖ

62.በአራተኛ ስንኝ ውስጥ የተጠቀሰት ነው እና ነበር ምንን ያመለክታል?

ሀ. ሕይወትን ለ. አሻራን ሐ. ዓለምን መ. ጊዜን



LIVEWORKSHEETS